ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረጀብ 24/1443 ሂ.
አውቃፍ ሚኒስቴር ፌብሯሪ 25/2022 ግ.

# የኢስራእ ሚዕራጅ ጎዞና የሶላት ግዴታነት

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ وَارْكَعُوا مَعَ الرَّاكِعِينَ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡
(ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፡፡ ዘካንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ፡፡ (ለጌታችሁ) ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሱ፡፡)

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል፡
የኢስራእና ሚእራጅ ጉዞዎች በፈጣሪ ስጦታዎችና አላህ (ዐ.ወ.) ይህን ህዝብ ከሌሎች ህዝቦች የለየባቸው በሆኑ በርካታ የጌታ ችሮታዎች የተሞሉ ነበሩ፡፡ ከነሱም እጅግ በጣም ታላቁ ያ ባሪያዎችን ከጌታቸው ጋር የሚያገናኘው የጌታ ቅን መምሪያ የሆነው የስግደት ግዴታነት ነበር፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በየቀንና ሌሊት የሚፈጸሙ አምሳ ስግደቶችን ግድ አደረገበኝ፡፡ ከዚያም ወደነብዩ ሙሳ በወረድሁ ጊዜ ጌታህ በህዝብህ ላይ ምን ግድ አደረገ በማለት ጠየቁኝ፡፡ እኔም እምሳ ስግደት በማለት መለስሁኝ፡፡ ተመለስ ጌታህን እንዳቀልልህ ጠይቅ፡፡ ምክንያቶም ህዝቦችህ ይህን ግዴታ መወጣት አይችሉምና አሉኝ፡፡ እኔም ጌታዬ ሆይ የህዝቦችን ግዴታ አቅልልኝ አልኩኝ አሉ፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጌታቸው (ሱ.ወ.) በየቀንና ሌለት የሚፈጸሙ አምስት ስግደቶች ናቸው ለያንዳንዱ ስግደትም አስር ስገደት አለው፡፡ ይህም አምሳ ስግደት ነው) እስካላቸው ጊዜ ድረስ መመላለሳቸውን አላቆሙም ነበር፡፡

በሚዕራጅ ሌሊት ከሰባቱ ሰማያት በላይ የሶላት ግዴታነት መደንገጉ የሶላት ደረጃ እጅግ የላቀና የሚይዘው ቦታ በጣም ከፍተኛ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ ሶላት የዓይን ማረፊያ፣ የልብ ሕይወትና የመንፈሶች ደስታ ምንጭ ነው፡፡ እሱም እምነታዊ እርገት ሲሆን ሰዎች ከዓለማቱ ጌታ ጋር ለሚኖራቸው ቅርበት መወጣጫ መሰላላቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَاسْجُدْوَاقْتَرِبْ}

(ስገድም፤ (ወደ አላህ) ተቃረብም፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አንድ በሪያ ከጌታው ጋ በጣም ቅርብ የሚሆነው በግንባሩ በሚደፋት ጊዜ ነው)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አደራህን በገንባር መደፋትህን አብዛ፡፡ ምክንያቱም አንተ አንድ ጊዜ በግባርህ መደፋትን አትደፋም በሱ አላህ አንድ ደረጃ ከፍ የሚያደርግህና ከአንተም አንድን ኃጢያት የሚሰርዝልህ ቢሆን አንጂ)፡፡

በሚዕራጅ ጉዞ ሶላት ግድ መደረጉ በዚያ የሐዘን ዓመት የሚል ስያሜ በተሰጠው ዓመት ለበርከታ ፈተናዎች ከተዳረጉ በኋላ ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የተቸረ የጭንቀት ማስወገጃ ስጦታ ነው፡፡ ይህም ስግደት

ቀልብን የሚያረጋጋ፣ ልብን የሚያሰፋ፣ ዓይንን የሚያረጋ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ሶላት በችግሮች ጊዜ አጋዥ እንድሆን ከአላህ (ዐ.ወ.) ለሰዎች የተቸረ ስጦታም ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.)እንድህ ይላል፡

**{وَلَقَدنَعْلَمُ أَنَّكَ يَضِيقُ صَدْرُكَ بِمَا يَقُولُونَ* فَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ وَكُنْ مِنَ السَّاجِدِينَ * وَاعْبُدْ رَبَّكَ حَتَّى يَأْتِيَكَ اليَقِينُ}**

(አንተም በሚሉት ነገር ልብህ የሚጠብ መኾኑን በእርግጥ እናውቃለን፡፡ ጌታህንም ከማመስገን ጋር አጥራው ከሰጋጆቹም ኹን፡፡ እውነቱም (ሞት) እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{ وَاسْتَعِينُوابِالصَّبْرِوَالصَّلاةِ}**

(በመታገስና በሶላትም ተረዱ፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ሶላት ለኔ የዓይን መርጊያ ተደረገለኛል)፡፡ ነብያችን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ለቢላል እንድህ ይሉ ነበር፡ (ቢላል ሆይ! ለሶላት ጥሪ አደርግ በሱም አሳርፈን)፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) ከሙሐመድ ህዝብ ሰግደትን ማቃለሉ ለፍጠረታት የአለውን እዝነት ምሉእነት የሚገልጽና ለዚህ ህዝብ የሰጠው ህግ በገርነት የተለየ፣ ሰቀቀንና ስቃይ የሌለበት ለመሆኑም መረጃ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{لاَ يُكَلِّفُ اللهُ نَفْسًا إِلاَّ وُسْعَهَا}**

(አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{يُرِيدُ اللّهُ بِكُمُ الْيُسْرَ وَلاَ يُرِيدُ بِكُمُ الْعُسْرَ}**

(አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በእናንተም ችግሩን አይሻም፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ሃይማኖትኮ ገር ነው)፡፡

እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አላህ አስጨናቂና አስቸጋሪ አድርጎ አላከኝም፡፡ ነገር ግን አስተማሪና አግሪ አደርጎ ነው የላከኝ)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልከተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡ ሶላት ሰዎችና ወደጌታቸው የሚያስተላልፉት የምስጢር ጥሪ መሆኑ ጥርጥር የለበትም፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ብሏል፡ ሶላትን ‹የመከፈቻ ምእራፍን› ከኔና ከባሪያ መካከል ወደሁለት ከፍያታለሁ፡፡ ለባሪያም የጠየቀውን እሰጠዋለሁ፡፡ አንድ ባሪያ {ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَالَمِينَ} ባለ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) ባሪያዬ አመሰገነኝ ይላል፡፡ እንድሁም {الرَّحْمَنِ الرَّحِيم} ባለ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) ባሪያዬ አሞገሰኝ ይላል፡፡ ከዚያም {مَالِكِ يَوْمِ الدِّين} ባለ ጊዜ አላህ (ዐ.ወ.) ባሪያ አወደሰኝ ይላል፡፡ እንድሁም {إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ} ባለ ጊዜ አላህ (ዐ.ወ.) ይህ ከኔና ከባሪያ መካከል ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ለባሪያም የጠየቀውን እሰጠዋለሁ ይላል፡፡ ከዚያም {اهْدِنَا الصِّرَاطَ ٱلْمُسْتَقِيمَ صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ ٱلْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلاَ الضَّالِّينَ} ባለ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ.) ይህ ለባሪያዬ ነው ለባሪያዬም የጠየቀውን እሰጠዋለሁ ይላል፡፡

ሶላት መንፈስን በመግራት፣ ጠባይን በማስተካከልና በመልካም ምግባር በመታነጽ ዘርፍ አስደናቂ ተስእኖ ያለው መሆኑ እንደዚሁ ጥርጥር የለበትም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وأقم الصلاة إِنَّ الصَّلَاةَ تَنْهَىٰ عَنِ ٱلْفَحْشَاءِ وَٱلْمُنْكَرِ}

(ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡) ስግደትን በትክክል የሚያደርስ ሰው፡ ውሸታም፣ አምታች፣ አታላይ፣ ክህደተኛ፣ በጀርባ አጥቂና ቃሉን የሚበላ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንም የአላህን መመሪያና ህግጋት መሰረት አድርጎ በምድር የሚንቀሳቀስ መልካም ምግባርና መልካም እሴት ይሆናል፡፡

ጌታችን ሆይ! እኛንና ዝርያዎቻችንንም ደንቡን ጠብቅን ሶላትን የምንሰገድ አድርገን፡፡ ጌታችን ሆይ! ጸሎታችንንም ተቀበለን፡፡ አሚን፡፡